# የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን

## የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የሥነ ምግባር መመሪያ ቁጥር 654/2013

### መግቢያ

የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን በሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 141/2000 በህዳር ወር 2000 ዓ.ም የተቋቋመ የመንግሥት የልማት ድርጅት ሲሆን የኮርፖሬሽኑ ዋነኛ ዓላማ ተሮካካሪና አቅምን ያገናዘበ የትራንስፖርት አገልግሎት መኖሩን ሚያጋግጥ የሚችል የተቀናጀ ከፍተኛ አቅም ያለው የባቡር ትራንስፖርት ሥርዓት ማዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በማኘቱ፣

በመላ ሀገሪቱ ዘመናዊ የባቡር መሠረተ ልማት በማንባት ወጪ ቆጣቢ፣ በአጭር ጊዜና በገፍ ጭነቶችን የሚጓጉዝ የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት በማስፋፋት የተማዘገበወን ፈጣን ኢኮኖሚዊ ዕድገት መደገፍ እና በመላ አገሪቱ የመንገደኞች የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ማስፋፋት ደግሞ ዕቅዶቹ እና ተልዕኮዎቹ በመሆናቸው፣

ይህን ዕቅድ ለማሳካት እና የተመደበወን በጀት በአግባቡ ለታለመለት ዓላማ እንዲወል ለማድረግ በሥነ ምግባር የታነፁና መሰናን እንዲሁም ከራይ ሰብሳቢነት አመለካከትን የሚፀየፉ የሥራ ኃላፊዎች፣ ባለሞያዎችና ሠራተኞች ያስፈልጋሉ፡፡ ሙስና፣ ብልሹ አሰራርና የሥነ ምግባር ግድፈት ፈጣን ጥራት ያለወና ወጪ ቆጣቢ የሆነ አገልግሎት እንዳይኖር በማድረግ የአንድን መ/ቤት ራዕይና ተልዕኮ የሚያደናቅፍ በመሆኑ፣

ሙስና፣ ብልሹ አሰራርና የሥነ ምግባር ግድፈት እንዳይኖር በመከተሚርና በመከላከል የኮርፖሬሽኑን ራዕይና ተልዕኮ ለማሳካት የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍል አሰራርን ለመወሰን በመመጣው በሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 144/2000 አንቀጽ 7 ንዐስ አንቀጽ (3) መሠረት ይህ የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የሥነ ምግባር መመሪያ ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የሥነምግባር መመሪያ ቁጥር654/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ወስጥ፡-

1. "**ኮሚሽን**" ማለት የፌደራል የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ነው፡፡
2. "**ኮርፖሬሽን**" ማለት የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን ነው፡፡
3. "**የሥራ ኃላፊ/ሜ**" ማለት በኮርፖሬሽኑ ወስጥ ዋናው ሥራ አስፈፃሚ ም/ዋና ሥራ አስፈፃሚዎች፣ ም/ሥራ አስፈፃሚ፤ የመምሪያ ኃላፊ/ዳይሬክተር፣ የአገልግሎት ዳይሬክተር፣ ሴክሽን ኃላፊ፣ ቡድን መሪ፣ የዋ/ሥ/አ/ጽ/ቤት ኃላፊ፣ የቢዝነስ ዩኒት ቡድን መሪ የዋና ሥ/አ/የቴክኒክ አማካሪ እና የቢዝነስ ዩኒት ማኝጀር የሆነ የሥራ ኃላፊ/ሜ ነው፡፡
4. "**ሠራተኛ**" ማለት በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 እና 494/98 አንቀጽ 4 መሠረት ከኮርፖሬሽኑ ጋር በቋሚ እና በኮንትራት ቅጥር ላይ የተመሠረተ የሥራ ግንኙነት ያለው ግለሰብ ነው፡፡
5. "**መመሪያ**" ማለት የኮርፖሬሽኑ የሥራ ኃላፊዎችና የሠራተኞች የሥነምግባር መመሪያ ማለት ነው፡፡
6. "**ሥነምግባር**" ማለት በእያንዳንዱ ተቋም ወይም ማኀበረሰብ ወስጥ ስህተት የሆኑት ድርጊቶች ወይም ተግባሮች እንዳይፈፀሙ ትክክል የሆኑት ደግሞ በቀና አስተሳሰብ እንዲፈፀሙ የሚያስችል ድርጊት ነው፡፡
7. "**የሥነምግባር መርሆ**" ማለት በአንድ ተቋም ወስጥ ጥሩና መጥፎ ድርጊቶች መደረግ ያለባቸውና የሌለባቸው ድርጊቶች የሚለጹበት አጠቃላይ የአስተሳሰብ፣ የአማካከት እና የተግባር አፈፃፀሞች የሚገኙበት ሥርዓት ማለት ነው፡፡
8. "**ደንብ**" ማለት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን አሠራር ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 144/2000 ማለት ነው፡፡
9. "**ቤተሰብ**" ማለት የኮርፖሬሽኑ የሥራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ የትዳር ጓደኛ ወይም በስሩ የሚተዳደር ዕድሜው 18 ዓመት ያልሞላ ልጅ ሲሆን ጋብቻ ሳይፈጽም እንደ ባልና ሚስት አብሮ የሚኖር ሰወን እና የጉዲፈቻ ልጅን ይጨምራል፡፡

10. ***"የቅርብ ዘመድ"*** ማለት የኮርፖሬሽኑ የሥራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ወላጆችን ተወላጆችን፣ እህቶችን፣ ወንድሞችን እና ሌሎች እስከ ሶስተኛ ደረጃ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያላቸው ሰዎችን ያጠቃልላል፡፡

11. ***"ተገቢ ያልሆነ ባህርይ/ተግባር"*** ማለት መንግሥት ከሚያወጣቸው አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች፣ ከኮርፖሬሽኑ አሠራርና መመሪያ እንዲሁም ተቀባይነት ካለው ልማዳዊ አሠራር ጋር የሚቃረን ወይም የሚጣጣም ማንኛውም አይነት ድርጊት ወይም ባህርይ ነው፡

12. ***"የሥነምግባር ብልሹነት"*** ማለት በዚህ መመሪያ ወስጥ የተጠቀሱትን የሥነምግባር መርሆዎችን የሚቃረን ድርጊት ወይም ባህርይ ነው፡

13. ***ሀብት"*** ማለት ማንኛውም የሚንቀሳቀስ ወይም የማይንቀሳቀስ ወይም ግዙፍነት ያለው ወይም የሌለው ንብረት ሲሆን የሜት ይዞታን፣ አዕምሯዊ እና ዕዳን ይጨምራል፡፡

14. ***"የጥቅም ግጭት"*** ማለት የሥራ ኃላፊው ወይም ሠራተኛው ወይም የቤተሰቡ ወይም የቅርብ ዘመዱ የገንዘብ ወይም ሌላ ዓይነት ጥቅም ከመደበኛው ሥራ ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ የሚጋጭ ወይም ግጭት ሊፈጥር የሚችል ሲሆን ነው፡

15. ***"ስጦታ"*** ማለት ለኮርፖሬሽኑ የሥራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ከሥራው ጋር በተያያዘ የሚሰጥ ወይም የተሰጠ ዋጋ ወይም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለው ማንኛውም ነገር ነው፡ ሆኖም ከባህል ወይም ከልምድ ጋር በተያያዘ በስራ ላይ ተጽዕኖ በማያሳድር ሁኔታ ግምታቸው ከብር 5 ሺህ (አምስት ሺ) የማይበልጥ አነስተኛ ዋጋ ያላቸው ድርጅቶችን ለማስተዋወቅ ወይም ደስታን ለመግለጽ የሚደረግ ስጦታን አይጨምርም፡

16. ***"ማስተንግዶ"*** ማለት ለኮርፖሬሽኑ የሥራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ወይም ለቤተሰቡ በሥራው ላይ እያለ የሚደረግለት ወይም የተደረገለት ነፃ የምግብ፣ የመጓጓዣ፣ የሆቴል፣ የመዝናኛ ወይም ሌላ ዓይነት አገልግሎት ነው፡

17. ***"ጥቆማ ማቅረብ ወይም ሪፖርት ማድረግ"*** ማለት በኮርፖሬሽኑ ወስጥ የተፈፀመን ሙስናና ብልሹ አሠራርን፣ የሥነምግባር ግድፈቶችን አስመልክቶ ለሥነምግባር መከታተያ ክፍል ወይም የፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ህግን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 943/2008 አንቀጽ 22 መሠረት ወንጀልን ለመመርመርና ለመክሰስ ሥልጣን ለተሰጠው አካል በአካል ወይም በስልክ ወይም በጽሁፍ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ የሚቀርብ ሚጃ ወይም የሚሰጥ አስተያየት ነው፡

18. ***"ሚስጥራዊ ሚጃ"*** ማለት አግባብ ባለው ህግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ መሠረት በሚስጥር እንዲጠበቅ የተደረገ ሚጃ ነው፡

19. ***"የሥነምግባር መከታተያ ክፍል"*** ማለት በኮርፖሬሽኑ የሥነምግባር ሁኔታን የሚያስተባብርና የሚያማክር አካል የሚገኝበት የሥራ ዘርፍ/አገልግሎት ነው፡

20. ***"የሥነምግባር መኮንን"*** ማለት በደንብ ቁጥር 144/2000 መሠረት ለሥነምግባር መከታተያ ክፍል የተሰጡትን ተግባራት የሚሰራ ኃላፊ ነው፡

21. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

## 3. የመመሪያው ዓላማ

1. በኮርፖሬሽኑ አሠራር ውስጥ የግልጽነትና ተጠያቂነት ባህልን በማዳበር አድልዎ የሌለበት መልካም አስተዳደር ማንባት፣
2. የህዝብ አገልጋይነትን ባህል በማዳበር ለኅብረተሰቡ ፍትሀዊ የሆነ አገልግሎት ማስጠት፣
3. በሥነ ምግባር የታነጸ ኃላፊና ሠራተኛ በማፍራትና መልካም ሥነ ምግባርን በማስፈን ወጤታማ ሥራ እንዲሰራ ማስቻል፣
4. የሥነ ምግባር ግድፈቶችን እንዳይፈፀሙ ማስገንዘብ፣ ተፈፅመው ሲገኙ የዕርምት ዕርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ሥርዓት ማዘርጋት ናቸው፡፡

## 4. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በኮርፖሬሽኑ እንዲሁም በአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ትራንዚት አገልግሎት የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## *5. የፆታ አገላለጽ*

በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

## *6. ኃላፊነት*

1. የዚህ መመሪያ ቅጂ በኮርፖሬሽኑ ወስጥ ለሚገኙ የሥራ ዘርፎች ተሰራጭቶ የሥራ ኃላፊዎች በሥራቸው ያሉት ሠራተኞች በሙሉ እንዲያወቁትና ተግባራዊ እንዲያደርጉት የሚድረግ ግዴታ አለባቸው፣
2. የሥነምግባር መኮንኑ በዚህ መመሪያ ወስጥ የተመለከቱትን የሥነምግባር መርሆዎችን አፈፃጸም በሚመለከት የሥራ ኃላፊዎችንና ሠራተኞችን የማማከር፣ የማስተማርና በኮርፖሬሽኑ ስላለው ሚልካም ሥነምግባር ሁኔታ በየጊዜው ሪፖርት የሚድረግ ኃላፊነት አለበት፣
3. የኮርፖሬሽኑ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ይህንን መመሪያ የማክበርና የሚፈፀም ግዴታ አለባቸው፣
4. የኮርፖሬሽኑ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ከሥነምግባር ጥሰት፣ ከሙስናና ብልሹ አሠራር ጋር የተያያዙ ድርጊቶች ሲፈጸሙ ለኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ ለሥነምግባር ማከታተያ ክፍሉ ወይንም ጉዳዩ ከባድ በሆነ ጊዜ ለፌደራል ፖሊስ የማስወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡

# <u>ክፍል ሁለት</u>

# <u>የሥነምግባር መርሆዎች</u>

## *7. ቅንነት (Integrity)*

የኮርፖሬሽኑ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች፡-

1. የሥራ አፈፃፀምና የግል ባህሪ ኅብረተሰቡ በኮርፖሬሽኑ ላይ ዕምነት እንዲያሳድር ሊያደርግ የሚያስችል መሆን ይኖርበታል፣
2. የኮርፖሬሽኑን ተልዕኮ፣ ራዕይና ዓላማዎች ማወቅ፣ በሕብረተሰበም ዘንድ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖር ጥረት ሚድረግ አለባቸው፣
3. ጥሩ ሥነምግባር በማሣየት ሥራቸወን በጥንቃቄ፣ በጥራት፣ በትጋት፣ በሙሉ ጉልበት፣ በብቃትና ወጤታማ በሆነ አኳኋን ማከናወን ይኖርባቸዋል፣
4. ከሕግ ወጭ ከማሥራት፣ ተገቢ ያልሆነ አድራጎት ከሚፈፀም ሚራቅ ይኖርባቸዋል፣
5. ለማቸወና ለስራቸው ጠቃሚ የሆኑ አስተያየቶችንና አሰራሮችን ከተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት ለመማር ዝግጁ መሆን አለባቸው፣
6. በስራ ቦታ ላይ ፆታዊ ትንኮሳ/ጥቃት እንዳይፈጸም ኃላፊነት መወጣት አለባቸው፣
7. የቅንነት መርሆዎችን ወይም በመርሆው ሥር የተዘረዘሩትን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች ሚፈጸም ያስቀጣል፣

ሀ. የኮርፖሬሽኑን ዝና የሚጎዳ ወይም ህዝቡ በኮርፖሬሽኑን ላይ የሚኖረውን ዕምነትና አክብሮት ዝቅ የሚያደርግ ባህሪ ማሳየት ወይም ተግባር መፈጸም፡፡

ለ. በአደንዛዥ ዕጽ በመሚዝ ወይም በአልኮል ማጠጥ ወይም በጫት ተጽዕኖ ምክንያት ሥራን ማከናወን አለመቻል፣

ሐ. ስራን በሚጠይቀው የሥነ ምግባር ደረጃ ተግባራትን አለማከናወን፣

መ. ከሥራ ባልደረቦች ጋር በመግባባት መሥራት ባለመቻል በሥራ ሂደት ላይ እንቅፋት መሆን፣

ሠ. በሥራ ቦታ ላይ ፆታዊ ትንኮሳ መፈጸም፡፡

ረ. በሥራ ቦታ ላይ ፆታዊ ጥቃት መፈፀም፡፡

## 8. ታማኝነት (Loyalty)

የኮርፖሬሽኑ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች፡ -

1. ለአገራቸው፣ ለሕገ-መንግሥቱ፣ ለኮርፖሬሽኑን፣ ለሥራ ኃላፊዎችና ለሥራ ባልደረቦቻቸው ታማኝ ሆነው መገኘት ይኖርባቸዋል፣
2. ሕገ-ወጥ ድርጊት ሚፈፀሙ ወይም ለፈፀም መታቀዱን ያወቁ የሥራ ኃላፊዎች ወይም ሠራተኞች በማንኛውም ጊዜ ለኮርፖሬሽኑ የበላይ ኃላፊ፣ ለሥነ ምግባር መኮንኑ ወይም ለሥነ ምግባርና ፀረሙስና ኮሚሽን ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፣
3. የሥራ ባልደረቦቹን ጥፋት ወይም ሥራቸውን በሚጠበቀው መደዊ ሥነ ምግባር መሠረት አለማከናወናቸውን እያወቁ መደበቅ ወይም መከላከል የለባቸውም፡፡
4. ከሥራ ኃላፊው የሚሰጡትን ሕጋዊ ትዕዛዞች የመፈፀም ኃላፊነት አለባቸው፣
5. በሥራ ኃላፊዎች ሙያዊ አስተያየት እንዲያቀርቡ በሚታዘዙበት ጊዜ ትክክለኛና ያልተዛባ አስተያየትን ያለሥጋት በቅንነት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፣
6. የኮርፖሬሽኑን ሃብት በጥንቃቄ በመያዝ ለተፈቀደው ተግባር ብቻ ማዋል ይኖርባቸዋል፣ የሥራ ሰዓትንም በአግባቡ በሥራ ላይ ማዋል ይጠበቅባቸዋል፣
7. የታማኝነት መርሆዎችን ወይም በመርሆው ሥር የተዘረዘሩትን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡ -

    ሀ. የሥራ ባልደረባን ህገ-ወጥ ድርጊት ወይም የሥነ ምግባር ጉድለት ወይም ተገቢ ያልሆነ አድራጎት ለአለቃው፣ ለሥነ ምግባር መኮንኑ ወይም ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ አለማሳወቅ፣ ወይም ቅን ልቦናን በሚቃረን ሁኔታ ጥቆማ ማቅረብ፣

    ለ. የመ/ቤቱን አገልግሎት ወይም ንብረት ወይም ገንዘብ ያላግባብ ማጠቀም ወይም ሌሎች እንዲጠቀሙ ማድረግ፣ ማጥፋ ወይም እምነት ማጉደል፣

    ሐ. በመ/ቤቱ የሥራ ሰዓት የግል ወይም ከኮርፖሬሽኑን ወጪ የሆነ የሌላ ሰው ሥራን ማከናወን፣

መ. ያለበቂ ምክንያት በሥራ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን ለሚመለከተው የሥራ ኃላፊ በወቅቱ አለማሳወቅ፣

ሠ. ከሥራው ጋር በተያያዘ ሥጦታ ወይም ማስተንግዶ መቀበል፣ ወይም ሥጦታ የሚቀበል የሥራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛን አይቶ አለመግለጽ፣

## 9. ግልጽነት (Transparency)

የኮርፖሬሽኑ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች፡-

1. የኮርፖሬሽኑ ደንበኞች የኮርፖሬሽኑን ዓላማ፣ የተለያዩ የአፈፃጸም መመሪያዎን እና የአሰራር ስርዓት እንዲያውቁ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር አለባቸው፣
2. አግባብ ባለው ህግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ መሠረት በሚስጥር ማጠበቅ ያለበት መረጃ ካልሆነ በስተቀር የኮርፖሬሽኑ ተገልጋዮች የሚፈልጉትን መረጃ ከማብራሪያ ጋር ማስጠት አለባቸው፣
3. ለሚሰጧቸው ውሣኔዎችና አገልግሎቶች ግልጽ መሆን፣ ተገልጋዮች አሟልተው ማማጣት ያለባቸውን ጉዳዮች አስቀድሞ በግልጽ ማስቀመጥና ማሳወቅ ይገባቸዋል፣
4. ተገልጋዮች በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ለሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች ወቅታዊና ተገቢ ማብራሪያ፣ ምላሽና መረጃ ማስጠት ይኖርባቸዋል፣
5. የግልጽነት መርሆዎን ወይም በመርሆው ስር የተዘረዘሩትን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈጸም ያስቀጣል፡፡

ሀ. ህጋዊ ለሆነ ጥያቄ በእጁ የሚገኘውን፣ ምስጢር ያልሆነንና ለህዝብ ግልጽ መድረግ ያልተከለከለ መረጃን ለማስጠት ፈቃደኛ አለመሆን፣

ለ. ለሚያስተላልፈው ውሣኔ ምክንያት ወይም ማብራሪያ ለማስጠት ፈቃደኛ አለመሆን፣

ሐ. ለሥራ ግምገማ አግባብነት ያለው አካል ላቀረበለት የመረጃ ጥያቄ በወቅቱ ምላሽ ለማስጠት ፈቃደኛ አለመሆን፣

መ. ከደንበኞችም ሆነ ከሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ለሚቀርቡ አገልግሎቶች ወይም ቅሬታዎች ተገቢውን ምላሽ በወቅቱ አለማስጠት፣

## 10. ምስጢር ጠባቂነት (Confidentiality)

የኮርፖሬሽኑ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች፡-

1. በስራ ጸባያቸው ምክንያት ወይም በሥራ አጋጣሚ ያወቋቸውንና ምስጢር የሆኑ የመ/ቤቱ ወይም ግላዊ የሆኑ መረጃዎችን መግለጽ የለባቸውም፣
2. ምስጢራዊ መረጃዎችን ለግል ጥቅማቸው አያውሉም፣

3. የምስጢር ጠብቂነት መርሆዎችን ወይም በመርሆው ስር የተዘረዘሩትን ግድታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈጸም ያስቀጣል፡ -

ሀ. ምስጢራዊ መረጃን ሆን ብሎ መግለጽ፣

ለ. ምስጢራዊ መረጃን በቸልተኝነት መግለጽ፣

ሐ. ምስጢራዊ መረጃን ለግል ጥቅም ማዋል፣

መ. ምስጢራዊ መረጃን ከጥቅም ውጭ ማድረግ ወይም ማጥፋት፣

## *11. ሐቀኝነት (Honesty)*

የኮርፖሬሽኑ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች፡ -

1. በቅንነት የመሥራት፣ የገቡትን ቃል የማክበር፣ ከማጭበርበር፣ ከማታለልና ከማስና ነፃ የመሆን ግዴታ አለባቸው፣
2. ስራን በመደበኛ የሥራ ጊዜ ወስጥ ማከናወን፣ አስቀድሞ የትርፍ ሰዓት ክፍያን በማሰብ ስራን አለማጓተት ወይም አለመዘፍ፣
3. የሐቀኝነት መርሆዎችን ወይም በመርሆው ስር የተዘረዘሩትን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈጸም ያስቀጣል፡ -

   ሀ. የማስና ወንጀል መፈጸም፣ ማጭበርበርና ማታለል፣

   ለ. ህግና መመሪያ ተከትሎ ስራውን በወቅቱ አለማከናወን፣

## *12. ተጠያቂነት (Accountability)*

የኮርፖሬሽኑ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች፡ -

1. ለሚሰጣቸው ውሣኔዎችና ለሚያከናወኗቸው ሥራዎች ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡ በውሣኔዎቻቸውና ባከናወኗቸው ሥራዎች ላይ ለሚቀርቡላቸው ተገቢ የሆነ የማጣራት ሥራ ራሳቸውን ዝግጁ የማድረግ፣ በተፈለጉ ጊዜ የመቅረብ ወይም የመገኘት ወይም ከሚጣራው ጉዳይ ጋር አግባብነት ያለውን መረጃ የማስጠት ግዴታ አለባቸው፣
2. የመንግሥት ፖሊሲዎችን፣ ህጎችንና ኮርፖሬሽኑ የሚያወጣቸውን መመሪያዎች የመፈፀም ግዴታ አለባቸው፣
3. ግዴታቸውን በአግባቡ ስለመወጣታቸው ተገቢው ጥያቄ ሲቀርብላቸው አስፈላጊውን ማብራሪያ ማስጠት ይኖርባቸዋል፣
4. የተጠያቂነት መርሆዎችን ወይም በመርሆው ስር የተዘረዘሩትን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡

   ሀ. ስላከናወኗቸው ሥራዎች ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ሪፖርት አለማቅረብ፣

ለ. የማግሥት ፖሊሲዎችን አዋጆችን ደንቦችንና መመሪያዎችን መሠረት አድርጎ መደበኛ ሥራን አለሚፈጸም ወይም ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ ሚፈጸም፤

ሐ. ስላከናወኗቸው ሥራዎች ለሚሟከተው አካል ሆን ብሎ የሚያሳስት ወይም ትክክል ያልሆነ ሪፖርት ማቅረብ፣

መ. የተሰጠን ግዴታ በወቅቱ አለመወጣት፣

### *13. የሕዝብን ጥቅም ማስቀደም (Serving the Public Interest)*

የኮርፖሬሽኑ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች፡ –

1. የሚያከናውኗቸው ሥራዎችና የሚሰጧቸው ውሣኔዎች የህዝብን ጥቅም የሚያስቀድም እንጂ የግላቸውን፣ የቤተሰባቸውን ወይም የቅርብ ዘመዶቻቸውን ጥቅም የሚያስቀድም መሆን የለባቸውም፡፡
2. በመንግሥት ሥራ ላይ እያሉ ከመደበኛ ሥራቸው ጋር ሊጋጭ የሚችል የውጭ ሥራ አይሰሩም፡፡
3. በሕግ ግዴታ ያለባቸው የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የራሳቸውንና የቤተሰቦቻቸውን ሀብትና ገንዘብ ማስመዝገብና ማሳወቅ አለባቸው፣
4. የህዝብን ጥቅም የማስቀደም መርሆዎችን ወይም በመርሆው ስር የተዘረዘሩትን ግዴታዎች በመተላፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈጸም ያስቀጣል፡ –
   - ሀ. የግል፣ የቤተሰብን፣ የቅርብ ዘመድን ጥቅም ከመ/ቤቱና ከኅብረሰተቡ ጥቅም ማስቀደም፡፡
   - ለ. በህግ ግዴታ እያለበት የራስንና የቤተሰብን ሀብት ለማስመዝገብ ፈቃደኛ አለመሆን ወይም ትክክለኛ ያልሆነ የሃብት ምዝገባ ማድረግ፣
   - ሐ. በመንግሥት ስራ ላይ እያለ ከመደበኛ ስራው ጋር ሊጋጭ የሚችል የውጭ ሥራ ማስራት፣

### *14. ሥልጣንን በአግባቡ ማጠቀም (Exercising Legitimate Authority)*

የኮርፖሬሽኑ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች፡ –

1. ሕግን፣ ደንብንና መመሪያን መሠረት በማድረግ ሥራቸውን ማከወን ይኖርባቸዋል፣
2. በሥልጣናቸው ያለአግባብ መገልገልና ሥልጣናቸውን የግል ጥቅም ለማግኘት ማዋል የለባቸውም፡፡
3. ሥልጣናቸውን ተጠቅመው በሥራቸው ያሉ ሠራተኞችን ከመመሪያና ደንብ ውጭ እንዲሰሩ ማዘዝና መገፋፋት የለባቸውም፡፡
4. ሥልጣንን በአግባቡ የማጠቀም መርሆዎችን ወይም በመርሆው ሥር የተዘረዘሩትን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈጸም ያስቀጣል፡ –
   - ሀ. ያለአግባብ ሥልጣንን በማጠቀም ማሠራት ወይም የአሠራር ሥርዓቶችንና ደንቦችን በማጣስ ማስራት፣
   - ለ. በበታች ሠራተኞች ላይ ጫና በመፍጠር ሠራኞች ሕገ–ወጥ ተግባር እንዲፈጽሙ ማዘዝ ወይም መፍቀድ፣
   - ሐ. ተገቢ ጥንቃቄ ሳያደርጉና የሌሎች ሰዎችን መብቶች ከግንዛቤ ሳያስገቡ ማስራት፣

### *15. አለማዳላት (Impartitality)*

የኮርፖሬሽኑ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች፡ –

1. ተገቢና ፍትሀዊ በሆነ አኳኋን ውሣኔ የማስጠት ግዴታ አለባቸው፣
2. በዘር፣ በጎሳ፣ በሃይማኖት፣ በፆታ፣ በጠፍ፣ በአካል ጉዳተኝነት፣ በዝምድና፣ በብሔር፣ በፖለቲካ ወይም በሚቻቸውም መቀራረብ ምክንያት አድልዎ ሚፈጸም የለባቸውም፣
3. ለሴቶችና አካል ጉዳተኞች የተደነገገውን ማበረታቻ ተግባራዊ ሚድረግ አለባቸው፣
4. የአለማዳላት መርሆዎችን ወይም በመርሆው ስር የተዘረዘሩትን ግዴታዎች በመተላለፍ ጥፋቶች ሚፈጸም ያስቀጣል፡-
    ሀ. የጉዳዩን ፍሬ ነገር እንዲሁም ህግንና መመሪያን ያላገናዘበ ውሣኔ ማስጠት ወይም ተገቢ ያልሆነ ሌላ ተመሳሳይ ድርጊት ፈጽሞ መገኘት፣
    ለ. ከሕግና መመሪያ ውጭ የሆነ ቅጥር፣ ዕድገት፣ ዕልጠና የትምህርት ዕድል ወዘተ ማስጠት፣
    ሐ. በትውውቅ፣ በፆታ፣ በብሔር፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በዝምድና ወይም አግባብነት በሌለው ግምት ምክንያት ልዩነት ሚድረግ፣
    መ. ለሴቶችና አካል ጉዳተኞች የተደነገገውን የማበረታቻ ትግበራ መጣስ፣

### *16. ሕግን ማክበር (Respecting the Law)*

የኮርፖሬሽኑ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች፡-

1. ሕገ-መንግሥቱን የማክበርና የማስከበር፣ አግባብነት ባላቸው ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ሥልጣን ባላቸው ኃላፊዎች በሚሰጡ ትዕዛዞች መሠረት ግዴታቸውን መወጣት አለባቸው፣
2. የሥራ ኃላፊዎች የሚሰጡት መመሪያ ወይም ትዕዛዝ ከህግ ውጭ መሆኑን ሲረዱ መመሪያውን ወይም ትዕዛዙን ለሰጠው ኃላፊ ማሳወቅ አለባቸው፣
3. በስራ ኃላፊዎች ሕገ-ወጥ የሆነ ትዕዛዝ እንዲፈጸም ከተደረገ ወዲያውኑ ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፣
4. የሥራ ኃላፊዎች ሕገ-ወጥ ወይም ተገቢ ያልሆነ መመሪያ ወይም ትዕዛዝ ለሠራተኞች ማስተላለፍ የለባቸውም፣
5. ሕግን የማክበር መርሆዎችን ወይም በመርሆው ስር የተዘረዘሩትን ግዴታዎች በመተላለፍ ጥፋቶች ሚፈጸም ያስቀጣል፡-
    ሀ. ሕጎችን፣ መመሪያዎችንና ትዕዛዞችን አለማክበር፣
    ለ. ሌሎች ሰዎችና ሠራተኞች ሕጋዊ የሆኑ ትዕዛዞችን እንዳያከብሩ መገፋፋት፣
    ሐ. ከሕግ ውጭ መሥራት ወይም በስሩ ያሉ ሠራተኞች ከሕግ ውጭ እንዲሰሩ መፍቀድ ወይም ማዘዝ፣
    መ. ከሥራ በመቅረቱ በሥራው ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑን እያወቀ የቅርብ የሥራ ኃላፊውን ሳያስፈቅድ ከአቅም በላይ ባልሆነ ምክንያት ከሥራ መቅረት፣

ሠ. በሥራ አካባቢ አምባጓሮ ወይም ጠበ ጫጠር ወይም ባለጉዳይ ወይም ኃላፊን ማስደብ ወይም መደባደብ፣

ረ. ለሥራው ተገቢ እንዳይሆን ሊያደርግ በሚችል ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ መገኘት፣

ሰ. የግዥ የሽያጭ እንዲሁም ሌሎች ገንዘብ ነክ ሥራዎችን በማንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት አለመፈጸም፡

ሸ. ያልተፈቀዱና በሕይወትና በንብረት ላይ አደጋ ሊያደርሱ የሚችሉ መሣሪያዎችን በመ/ቤቱ ቅጥር ግቢ ወስጥ ይዞ መገባት፣

ቀ. በመ/ቤቱ ቅጥር ግቢ ወስጥ እንዲገቡ የሚፈቀዱ ነገሮችን ይዞ መግባት፣

## *17. ለሕዝብ ጥያቄ ተገቢወን ምላሽ ማስጠት (Responsiveness)*

የኮርፖሬሽኑ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች፡ -

1. ባለጉዳዮችን በአክብሮትና በትህትና በመቀበል፣ በጥሞና በማድመጥ ለጥያቄዎቻቸው ተገቢወን ምላሽ ወይም መፍትሄ በወቅቱ ማስጠት ይኖርባቸዋል፣
2. ለባለጉዳዮች ወይም ሠራተኞች ስለ መ/ቤቱ አሠራር ሥርዓት ያልተዛባና ትክክለኛ መረጃ ማስጠት ይኖርባቸዋል፣
3. ለሕዝብ ጥያቄ ተገቢወን ምላሽ የማስጠት መርሆዎችን ወይም በመርሆው ስር የተዘረዘሩትን ግዴታዎች በመተላለፍ ጥፋቶች መፈጸም ያስቀጣል፡ -

   ሀ. ለባለ ጉዳይ ተገቢ ትህትና አለማሳየት ወይም ተገቢ ባልሆነ አኳኋን ማስተናገድ፣

   ለ. ተገልጋይ/ደንበኛ መብቱን በሚመለከት የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲይዝ ማድረግ፣ በኮርፖሬሽኑ ላይ ቅሬታ እንዲያደርበት ወይም አለመግባባት እንዲፈጠር ማድረግ፣

   ሐ. ተገልጋዮች ለሚያቀርቡት ጥያቄ ወቅታዊና ተገቢ ምላሽ አለማስጠት፣

## *18. አርአያነት (Exercising Leadership)*

የኮርፖሬሽኑ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች፡ -

1. የመንግሥት ሥራ በሚያከናወኑበት፣ በማኅበረሰቡ ወስጥ በሚኖሩበት ጊዜ ግንባር ቀደምና ምሣሌ በመሆን የሚጠበቅባቸወን ከፍ ያለ አርአያነት በማሳየት በዚህ ደንብ ወስጥ የተመለከቱትን መርሆዎች ማክበልትና በተግባር እንዲተረጉሙ ማገዝ ይኖርባቸዋል፣
2. የኃላፊነት ስሜቱ የሚሰማቸው፣ የተሻለ ለወጥን የሚያግፉ፣ የኮርፖሬሽኑን መልካም ስም የሚጠብቁና የአሰራር ባህል እንዲዳብር፣ መተማመን ሥር እንዲሰድና ፀንቶ እንዲቆይ የሚያደርጉ መሆን አለባቸው፣

3. የአርአያነት መርሆዎችን ወይም በመርሆው ስር የተዘረዘሩትን ግዴታዎች በመተላለፍ ጥፋቶችን መፈጸም ያስቀጣል፣

ሀ. የሥራ ኃላፊንና ሌሎች ሠራተኞችን መልካም ሥነ ምግባር በተላበሰ መልኩ አለማስተናገድ፣

ለ. የኮርፖሬሽኑን ስምና ዝና የሚያጎድፍ ተግባር ፈጽሞ መገኘት፣

ሐ. የኮርፖሬሽኑን የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የሥራ ተነሳሽነት የሚቀንስ ወይም በሰራተኞች መካከል አለመግባባትን የሚፈጥር ድርጊት መፈጸም፡፡

## ክፍል ሦስት

## በዲሲፕሊን የሚያስቀጡ የሥነ ምግባር ጥፋቶችና የእርምጃ አወሳሰድ ዝርዝር

### 19. የዲሲፕሊን ቅጣት ዓላማና አፈፃፀም

1. በኮርፖሬሽኑ የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ላይ የሚወሰደው የዲሲፕሊን እርምጃ ዓላማው፣ የሥራ ኃላፊው ወይም ሠራተኛው በፈጸመው ጥፋት ተጸጽቶ እንዲታረምና ለወደፊቱም ሥራውን በሚገባ ምግባር ለማከናወን እንዲችል ለማስተማርና የማይታረም ሆኖ ሲገኝ ከስራው እንዲሰናበት ለማድረግ ነው፡፡
2. በኮርፖሬሽኑ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ላይ የሚወሰደው የዲሲፕሊን እርምጃ አፈፃጸም፡-
   - ሀ. የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ሥራቸውን በአግባቡ ባለሟጸማቸው ወይም ማድረግ የማይገባቸውን በማድረጋቸው ስለጥፋታቸው በፍትሐ ብሔር ወይም በወንጀል ተጠያቂነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ላደረሱት ጥፋት ወይም የዲሲፕሊን ጉድለት መ/ቤቱ ባለው የሥነ ምግባር መመሪያ፣ የሕብረት ስምምነት፣ የአስተዳደር መመሪያ ወይም የሥራ ኃላፊዎች መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ተገቢው አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድባቸዋል፣
   - ለ. በሥነ ምግባር ግድፈት የሚወሰነው ቅጣት ማንኛውም ፍርድቤት የሚሰጠውን ውሣኔ ሳይጠበቅ ሊፈጸም ይችላል፣
   - ሐ. የሥነ ምግባር ግድፈት የፈጸመ ማንኛውም የሥራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ድርጊቱ በዚህ የሥነ ምግባር መመሪያ፣ በሕብረት ስምምነት፣ በአስተዳደር መመሪያ እና በሥራ ኃላፊዎች መተዳደሪያ ደንብ ላይ የተመለከተ ሆኖ ሲገኝ በአንድ ጊዜ በሁሉም በተደራራቢነት ሊቀጣ አይገባውም፡፡

## *20. የዲሲፕሊን ቅጣት ዓይነቶችና አመዳደብ*

*ሀ/*

1. የቃል ማስጠንቀቂያ፣
2. የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ፣
3. እስከ አንድ ወር በሚደርስ የደመዎዝ ቅጣት፣
4. እስከ ሦስት ወር የሚደርስ የደመዎዝ ቅጣት፣
5. እስከ ሁለት ዓመት ሊቆይ የሚችል  ከሥራ ደረጃና ከደመወዝ ዝቅ ማድረግ፣
6. ከሥራ ማስናበት፣

ለ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሀ(ከ1-3) የተዘረዘሩት ቀላል የዲስፕሊን ቅጣቶች ሲሆኑ፣ (ከ4-6) የተዘረዘሩት ከባድ የዲስፕሊን ቅጣቶች ናቸው፡፡

ሐ/ ቀላል ጥፋቶችን በተደጋጋሚ መፈጸም ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት ሊያስከትል ይችላል፡፡

## 21. የሥነምግባር ጉድለት አይነቶችና የጥፋት ደረጃ

ከታች በሰንጠረዥ የተገለጸው በእያንዳንዱ ሚሆ ስር የተቀመጡ የሥነምግባር ጉድለቶችን እንደ ጥፋት ደረጃቸው በቀላልና በከባድ የዲስፕሊን ጥፋት የተመደቡ መሆናቸውን ለማሳየት የቀረበ ነው፡፡

| ተ.ቁ | አንቀጽ | ን.አንቀጽ | በቀላል የዲስፕሊን ጥፋት የተመደቡ | በከባድ የዲስፕሊን ጥፋት የተመደቡ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | 7 | 7/7 | ሐ/ ሥራው በሚጠይቀው የሥነምግባር ደረጃ ተግባራትን አለማከናወን፣<br>መ/ ከሥራ ባልደረቦቹ ጋር በመግባባት መሥራት ባለመቻል በሥራ ሂደት ላይ እንቅፋት መሆን፣<br>ሠ/ በመ/ቤቱ ወስጥ ዕታዊ ትንኮሳ ሚፈጸም፣ | ሀ/ የመ/ቤቱን ዝና የሚጎዳ ወይም ህዝቡ በመ/ቤቱ ላይ የሚኖረውን እምነትና አክብሮት ዝቅ የሚያደርግ ባህሪ ማሳየት ወይም ተግባር ሚፈጸም፣<br>ለ/ በአደንዛዥ ዕጽ በመሚዝ ወይም በአልኮል ማጠጥ ወይም በጫት ተጽዕኖ ምክንያት ሥራን ማከናወን አለመቻል፣<br>ሐ/ በመ/ቤቱ ወስጥ ፆታዊ ጥቃት ሚፈጸም፣ |
| 2. | 8 | 8/7 | ሐ/ በመ/ቤቱ የሥራ ሰዓት የግል ወይም ከመ/ቤቱ ስራ ውጭ የሆነ ሌላ ሥራን ማከናወን፣<br>መ/ ያለበቂ ምክንያት በሥራ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን ለሚመለከተው ኃላፊ በወቅቱ አለማሳወቅ፣ | ሀ/ የሥራ ባልደረባን ህገ-ወጥ ድርጊት ወይም የሥራ ሥነምግባር ጉድለት ወይም ተገቢ ያልሆነ አድራጎት ለአለቃው፣ ለሥነምግባር መኮንኑ ወይም ለመ/ቤተ የበላይ ኃላፊ አለማሳወቅ ወይም ቅን ልቦናን በሚቃረን ሁኔታ ጥቆማ ማቅረብ፣<br>ለ/ የመ/ቤቱን አገልግሎት ወይም ንብረት ወይም ገንዘብ ያላግባብ ማጠቀም ወይም ሌሎች እንዲጠቀሙ ማድረግ፣ ማጥፋት ወይም እምነት ማጉደል፣<br>ሠ/ ከሥራው ጋር በተያያዘ ሥጦታ ወይም ማስተንግዶ መቀበል፣ ወይም ሥጦታ የሚቀበል ሠራተኛ አይቶ አለመግለጽ |
| 3. | 9 | 9/5 | ሀ/ ህጋዊ ለሆነ ጥያቄ በእጁ የሚገኘውን ሚስጢር ያልሆነንና ለህዝብ ግልጽ ሚድረግ ያልተከለከለን ሚጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን፣<br>ለ/ ለሚያስተላልፈው ወሳኔ ምክንያት ወይም ማብራሪያ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን፣ | |

| ተ.ቁ | አንቀጽ | ን.አንቀጽ | በቀላል የዲስፕሊን ጥፋት የተመደቡ | በከባድ የዲስፕሊን ጥፋት የተመደቡ |
|---|---|---|---|---|
| | | | ሐ/ ለሥራ ግምገማ አግባብነት ያለው አካል ላቀረበለት የመረጃ ጥያቄ በወቅቱ ምላሽ ለማስጠት ፈቃደኛ አለመሆን፣<br>መ/ ከባለ ድርሻ አካላት፣ ከደንበኞችም ሆነ ከሠራተኞች ለሚቀርቡ አገልግሎቶች ወይም ቅሬታዎች ተገቢውን ምላሽ በወቅቱ አለማስጠት፣ | |
| 4. | 10 | 10/3 | ለ/ ምስጢራዊ መረጃን በቸልተኝነት መግለጽ፣ | ሀ/ ምስጢራዊ መረጃን ሆን ብሎ መግለጽ፣<br>ሐ/ ምስጢራዊ መረጃን ለግል ጥቅም ማዋል፣<br>መ/ ምስጢራዊ መረጃን ከጥቅም ውጭ ማድረግ ወይም ማጥፋት፣ |
| 5. | 11 | 11/3 | | ሀ/ የማሽና ወንጀል መፈጸም፤<br>ለ/ ህግና መመሪያ ተከትሎ ስራን በወቅቱ አለማከናወን፣ |
| 6. | 12 | 12/4 | ሀ/ ስላከናወኗቸው ሥራዎች ለሚቆጣጠራቸው አካል በወቅቱ ሪፖርት አለማቅረብ፣<br>መ/ የተሰጠን ግዴታ በወቅቱ አለመወጣት፣ | ለ/ የማንግሥት ፖሊሲዎችን፣ አዋጆችን፣ ደንቦችን፣ መመሪያዎችን መሠረት አድርጎ መደበኛ ሥራን አለመፈፀም ወይም ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ መፈጸም፤<br>ሐ/ ስላከናወኑዋቸው ሥራዎች ለሚቆጣጠሯቸው አካላት ሆን ብሎ የሚያሳስት ወይም ትክክል ያለሆነ ሪፖርት ማቅረብ፣ |
| 7. | 13 | 13/4 | | ሀ/ የግልን፣ የቤተሰብንና የቅርብ ዘመድን ጥቅም ከመ/ቤቱና ከኅብረተሰቡ ጥቅም ማስቀደም፤<br>ለ/ በሕግ ግዴታ እያለበት የራስንና የቤተሰብን ሀብት ለማስመዝገብ ፈቃደኛ አለመሆን ወይም ትክክለኛ ያልሆነ የሃብት ምዝገባ ማድረግ፣<br>ሐ/ በመንግሥት ስራ ላይ እያለ ከመደበኛ ስራው ጋር ሊጋጭ የሚችል የውጭ ሥራ ማስራት፣ |

| ተ.ቁ | አንቀጽ | ን.አንቀጽ | በቀላል የዲስፕሊን ጥፋት የተመደቡ | በከባድ የዲስፕሊን ጥፋት የተመደቡ |
|---|---|---|---|---|
| 8. | 14 | 14/4 | ሐ/ ተገቢ ጥንቃቄ ሳያደርጉና የሌሎች ሰዎችን መብቶች ከግንዛቤ ሳያስገቡ ማስራት፣ | ሀ/ ስልጣንን ያላግባብ በማጠቀም ማስራት ወይም የአሰራር ሥርዓቶችንና ደንቦችን በመጣስ ማስራት፣<br>ለ/ በበታች ሠራተኞች ላይ ጫና በመፍጠር ሠራተኞች ሕገ-ወጥ ተግባር እንዲፈጽሙ ማዘዝና መፍቀድ፣ |
| 9. | 15 | 15/4 | መ/ ለሴቶችና አካል ጉዳተኞች የተደነገገወን የሚበረታቻ ትግበራ መጣስ፣ | ሀ/ በቸልተኝነት የጉዳዩን ፍሬ ነገር እንዲሁም ህግንና መመሪያን ያላገናዘበ ውሣኔ ማስጠት ወይም ተገቢ ያልሆነ ሌላ ተመሳሳይ ድርጊት ፈጽሞ ማገኘት፣<br>ለ/ ከሕግና መመሪያ ውጭ የሆነ ቅጥር፣ ዕድገት፣ ሥልጠና የትምህርት ዕድል ወዘተ ማስጠት፣<br>ሐ/ በትወልድ፣ በፆታ፣ በብሔር፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በዝምድና ወይም አግባብነት በሌለው ግምት ምክንያት ልዩነት ማድረግ፣ |
| 10. | 16 | 16/5 | ለ/ ሌሎች ሰዎችና ሠራተኞች ህጋዊ የሆኑ ትዕዛዞች እንዳያከብሩ ማነፋፋት፣<br>ቀ/ በመ/ቤቱ ቅጥር ግቢ ወስጥ እንዲገቡ የማይፈቀዱ ነገሮች ይዞ መግባት፣ | ሀ/ ህጎችን፣ መመሪያዎችንና ትዕዛዞችን አለማክበር፣<br>ሐ/ ከሕግ ውጭ ማሠራት ወይም በሥሩ ያሉ ሠራተኞች ከሕግ ውጭ እንዲሰሩ፣ መፍቀድ ወይም ማዘዝ፣<br>መ/ ከሥራ በመቅረቱ በሥራው ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑን እያወቀ የቅርብ የሥራ ኃላፊወን ሳያስፈቅድ ከአቅም በላይ ባልሆነ ምክንያት ከሥራ መቅረት፣<br>ሠ/ በሥራ አካባቢ አምባጓሮ ወይም ጠብ መፍጠር ወይም ባለጉዳይን ወይም የሥራ ኃላፊን ማስደብ ወይም መደባደብ፣<br>ረ/ ለሥራው ተገቢ እንዳይሆን ሊያደረግ በሚችል ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ማገኘት፣<br>ሰ/ የግዥና የሽያጭ እንዲሁም ሌሎች ገንዘብ ነክ ሥራዎችን በማንገሥት |

| ተ.ቁ | አንቀጽ | ን.አንቀጽ | በቀላል የዲስፕሊን ጥፋት የተመደቡ | በከባድ የዲስፕሊን ጥፋት የተመደቡ |
|---|---|---|---|---|
| | | | | ደንብና መመሪያ መሠረት አለሜጸም.<br>ሸ/ ያልተፈቀዱና በህይወትና በንብረት ላይ አደጋ ሊያደርሱ የሚችሉ መሣሪያዎችን በመ/ቤቱ ቅጥር ግቢ ይዞ መግባት፣ |
| 11. | 17 | 17/3 | ሀ/ ለባለ ጉዳይ ተገቢ ትህትና አለማሳየት ወይም ተገቢ ባልሆነ አኳኋን ማስተናገድ፣<br>ሐ/ ተገልጋዮች ለሚያቀርቡት ጥያቄ ወቅታዊና ተገቢ ምላሽ አለማስጠት፣ | ለ/ ተገልጋይ/ ደንበኛ መብቱን በሚጻከት የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲይዝ ሜድረግ፣ ኮርፖሬሽኑ ላይ ቅሬታ እንዲያደርበት ወይም አለመግባት እንዲፈጠር ሜድረግ፣ |
| 12. | 18 | 18/3 | ሀ/ የሥራ ኃላፊንና ሌሎች ሠራተኞችን ሜልካም ሥነምግባርን በተላበሰ ሜልኩ አለማስተናገድ፣ | ለ/ የኮርፖሬሽኑን ስምና ዝና የሚያጎድፍ ተግባር ፈጽሞ ማኘት፣<br>ሐ/ የኮርፖሬሽኑን ሠራተኞች የሥራ ተነሳሽነት የሜቀንስ ወይም በሰራተኞች መካከል አለመግባባት የሜፈጥር ድርጊት ሜፈጸም፡፡ |

## 22. የዲስፕሊን ኮሚቴና የክስ አመሰራረት

1. ቀላል የዲስፕሊን ጥፋት ተፈጽሞ ሲገኝ የቅርብ የሥራ ኃላፊው በኮርፖሬሽኑ የአስተዳደር መመሪያ መሠረት ቅጣት ይወስናል፤

2. በዚህ መመሪያ የተጠቀሱትን የሥነምግባር ጉድለቶች አይቶ የውሳኔ ሃሳብ የሚቀርብ የዲሲፕሊን ኮሚቴ አመሰራረትና አሰራር በሕብረት ስምምነት፣ በአስተዳደር መመሪያና በሥራ ኃላፊዎች መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ይሆናል፣

3. የይግባኝ አቀራረብና የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር የሚሆነው ለኃላፊዎች በሥራ ሜዎች መተዳደሪያ ደንብ፣ ለሠራተኞች ደግሞ በኅብረት ስምምነት ወይም በአስተዳደር መመሪያ መሠረት ይሆናል፡፡

4. አንድ ጥፋት በዚህ መመሪያ፣ በሕብረት ስምምነት ወይም በአስተዳደር መመሪያ እንዲሁም በሥራ ሜዎች መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የሚያስቀጣ ሆኖ ሲገኝ ለሠራተኞች በሕብረት ስምምነት ወይም በአስተዳደር መመሪያው፣ ለሥራ ኃላፊዎች በሥራ ሜዎች መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 23. ጥቆማ ስለማቅረብ

ሀ. ማንኛውም ሠራተኛ በዚህ መመሪያ ወስጥ የተካተቱ መርሆዎችን የሚፃረር የሥነምግባር ጉድለት ሲፈፀም በማንኛውም መንገድ ካወቀ ወይም ከተመለከተ ጉዳዩን ለኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፤ ለሥነምግባር መከታተያ ክፍሉ፣ ከበድ ያለ ከሆነም ለፌዴራል ፖሊስ ማሳወቅ አለበት፣

ለ. የሚቀርበው ጥቆማ እውነተኛ፣ ያልተዛባ፣ ከበቀል የፀዳ፣ አሳሳች ያልሆነና ምክንያታዊ በሆነ እምነት ላይ የተመሰረተ መሆን ይኖርበታል፣

ሐ. ጥቆማ አቅራቢው ከማንኛውም በቀል ጥቃት የመጠበቅ መብት አለው፣

መ. ጥቆማ አቅራቢው ማንነቱ እንዳይገለጽ ከፈለገ በምስጢር የሚያዝለት ይሆናል፣

## 24. የኃላፊነትና የመተባበር ግዴታ

ሀ. ሁሉም የሥራ ኃላፊዎች በስራቸው ያሉ ሠራተኞች የሥነምግባር መመሪያውን እንዲያውቁት የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፣

ለ. ማንኛውም ሠራተኛ፣ የሥራ ኃላፊና የሥራ ክፍል የሥነምግባር መከታተያ ክፍሉ ለሥራው የሚፈልገውንና የሚጠይቀውን መረጃና አስፈላጊ ድጋፍ በተጠየቀ ጊዜ የመስጠት ግዴታ አለበት፣

## 25. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

*ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት የለውም፡*

## 26. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## 27. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከዛሬ ...............ቀን ............... ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

*ብርሃኑ በሻህ (ዶ/ር)*

*የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን*

*ዋና ሥራ አስፈፃሚ*

*2010 ዓ.ም*

*<u>አዲስ አበባ</u>*